# ማ ው ጫ

ስርዓተ ቤተክርስቲያን ....... 2
የቤተክርስቲያን ትርጉም ....... 3
የቤተ ክርስቲያን አሠራርና ክፍሎች ....... 3
ሀ/ የቤተ ክርስቲያን አሠራር ....... 3
ለ/ የቤተክርስቲያን ክፍሎች ....... 3
ንዋያተ ቅድሳት ....... 4
1 የቤተ መቅደስ ንዋያተ ቅድሳት ....... 4
የቀሳውስት አልባሳት ....... 4
የዲያቆናት ልብስ ....... 4
2 የቅኔ ማኅሌት ንዋያተ ቅድሳት፡ ....... 5
፩ ጾም ....... 6
፲ቱ የአዋጅ አጽዋማት ....... 6
የማይጾምባቸው ጊዜያት ....... 6
የሚበሉ የማይበሉ እንስሣት ....... 6
የሚበሉ እንስሳት ....... 7
የማይበሉ እንስሳት ....... 7
፪ ጸሎት ....... 7
፯ቱ የጸሎት ጊዜያት ....... 7
የግል ጸሎት ....... 8
የጋራ ጸሎት ....... 8
የምንጸልያቸው የጸሎት ዓይነቶች ....... 8
፫ ስግደት ....... 8
ለ/የስግደት ዐይነቶች ....... 8
1 የአምልኮ ስግደት ....... 9
2 የጸጋ ስግደት ....... 9
የሚሰገድባቸው ጊዜያት ....... 9
የማይሰገድባቸው ጊዜያት ....... 9
....... 10
ማማተብ ....... 10
ቤተክርስቲያን ስንገባ ማድረግ ያለብን ....... 11
ሥ ላ ሴ ....... 11
፬ ምጽዋዕት ....... 12

# ትምህርተ ሃይማኖት

ትምህርተ ሃይማትን ሊቃውንቱ በሁለት ከፍለው እንደሚያስተምሩትና እንሚያስረዱት እኛም እንዲሁ በሁለት ከፍለን እንመልከተው፡፡

***ዶግማ*፡-** ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም እምነት ማለት ነው፡፡ ዶግማ ወይም እምነት አይጨመርበትም፣ አይቀነስለትም፣ አይሻሻልም፣ አይለወጥም፡ ከጊዜው ጋር ስላልሄደ፣ ስላልተስማማን፣ አስቸጋሪ ስለሆነ ወዘተ በሚል ማንኛውም ምክንያት መሻሻል መለወጥ መጨመር መቀነስ የለበትም ለምሳሌ ያህል ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ፤ ቢመረምር እንጂ የማይመረመር ሁሉን ቻይ አምላክ፤ የሚሳነው ነገር የሌለ ፈጣሪ፤ የሰማይና የምድር ባለቤት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔር ነ ። እግዚአብሔር (ፈጣሪ) የአካል ሦስትነት አለው፡፡ በመለኮት፣ በመፍጠር፣ በሥልጣን፣ በአገዛዝ፣ በፈቃድ ግን አንድ ነው፡፡ በሦስትነቱ አብ፤ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሲባል በአንድነቱ አንድ መለኮት አንድ እግዚአብሔር ይባላል፡፡/ጸሎተ ሃይማኖት/

**ቀኖና፡-** ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙ ሥርዓት ማለት ነው፡፡በእምነታችን ለመጽናት እምነታችንን ጠብቀን ለመቆየት ሥርዓት ያስፈልገናል፡፡ ሁሉም የመሠለውን የሚያደርግበት መሆን የለበትም፡፡ ይህ ሥርዓት ግን ሊጨመርበት፣ ሊሻሻል፣ ሊቀነስ የሚችል ነው፡፡ ነገር ግን ሁኔታውን አይቶ ማሻሻል የሚችለው ቅዱስ ሲኖዶስ ብቻ ነው፡፡

**እግዚአብሔር:** እግዚአብሔር የሚለው ቃል ከግዕዝ የተገኘ ሲሆን "እግዚእ" ማለት ጌታ ማለት ነው፡፡ "ብሔር" ማለት ደግሞ ዓለም ማለት ነው፡፡

**እምነት** ማመን ማለት ስለእግዚአብሔር የሰሙትንና የተረዱትን እንዲሁም የተቀበሉትን ትምህርት እውነት ነው ብሎ በልብ መቀበል ነው (ሮሜ 10፡17)፡፡ እምነት እግዚአብሔር የገለጠውን እውነት (ሃይማኖት) አዎ እውነት ነው ትክክል ነው ብሎ "አሜን" ብሎ መቀበል ነው።

***መታመን*** መታመን ሲባል እግዚአብሔር የሰጠው ቃልና እውነት ተስፋ ለእኔም ይሆንልኛል ይደረግልኛል እርሱ ያድነኛል ይመግበኛል ብሎ ሙሉ ተስፋንና ተአምኖን እሱላይ ማድረግ ነው።ደግሞ ያመኑትንና የተቀበሉትን እምነት በሰው ፊት ሳይፈሩና ሳያፍሩ መመስከር ነው፡፡***መታመንን*** ፥ ተግባራዊ ምላሽ መስጠትን ያሳያል

**ሃይማኖት** ማለት ለዓለም ፈጣሪ አለው ብለው የሚያምኑት እምነት ነው፡፡ ለዓለም ፈጣሪ አለው ብለው የሚመሰክሩት ቃል ነው፡፡ ሃይማኖት ሰው ፈጣሪውን የሚያመልክበት፣ የእግዚአብሔር ልጅ የሚሆንበት፣ ጽድቅንም የሚሠራበት፣ የዘላለም ሕይወትን የሚያገኝበት መንገድ ነው፡፡

## ስርዓተ ቤተክርስቲያን

***ሥርዓት*** ማለት "ሠርዐ" ሠራ ደነገገ ደንብ አወጣ ከሚለው የግዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙ ሕግ ደንብ አሠራር መርሐ ግብር ማለት ነው፡፡ስለዚህ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን በሚገባ ያወቁ ክርስቲያኖች የቤተክርስቲያንን መሠረታዊ እውቀት እና ትርጓሜ ምንነት በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ንዋያተ ቅድሳት ማድረግ የሚገባውን ክብርና ጥንቃቄ ያውቃሉ፡፡

ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ስንል የቤተክርስቲያን እቅድ የቤተክርስቲያን አሠራር መርሐ ግብር ወይም ደምብ ማለታችን ነው።

ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ስንል ሕንፃውን፣ ምዕመኑን ጉባኤውን (ሶስቱንም) የሚያመላክት ሥርዓት ማለታችን ነው፡፡ (የቤተክርስቲያን ትርጉም ተመልከት )

ሥርዓት መዕመናን አንድ ኣሳብና አንድ ልብ እንዲሆኑ ይረዳል ፤ያለ አንድ አይነት ሥርዓት አንዱ ሲጀምር አንዱ የሚጨርስ አንዱ ሲዘምር ሌላው የሚያስተምር ከሆነ መለያየትን ያመጣል፡፡

ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በመሰረተ እምነት (ዶግማ) የምናምንባቸውን በተግባር የምንገልጽበት መንገድ ወይንም አምነትን በተግባር የምናሳይበት /ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።ያዕ 2፤16/
መንገድ ነው፡፡አነዚህ በተግባር የምንፈጽማቸው ነገሮች አንደሚከተሉት ናቸው።

**፩** ጾም

**፪** ጸሎት

**፫** ስግደት

**፬** መስዋእት ናቸው።

# የቤተክርስቲያን ትርጉም

## 1 ቤተክርስቲያን ህንጻ

ቤተክርስቲያን ማለት አምልኮተ እግዚአብሔር የምንፈጽምበት **ሕንጻ ቤተክርስቲያን** ይህም የክርስቲያኖች መሰብሰቢያ መገናኛ፤ ክርስቲያኖች በአንድነት ተሰብስበው የሚጸልዩበት ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉበት የሚሰግዱበት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት የጸሎት ቤት ማለት ነው፡፡

## 2 ቤተክርስቲያን ምዕመን

ቤተ ክርስቲያን ደግሞ "አሐቲ ጉባኤ" እንዲል የምእመናን ስብስብ ስለኾነች የራሷ ሕግ አላት

ቤተክርስቲያን ማለት የክርስቲያን ወገን፣ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ (የምእመናን አንድነት ጉባኤ) የሚጠራበት ስም

## 3 ቤተክርስቲያን ሰውነት

ቤተክርስቲያን ሲል የሚወክለው ምእመናንን ነው ክርስቲያኖች የክርስቶስ ማደሪያዎች ናችውና ቤተክርስቲያን ማለት የክርስቶስ ማደሪያ የሆኑ ክርስቲያኖችን /የክርስቲያኖችን ሰውነት/ የሚያመለክት ነው፡፡ 1ኛቆሮ.3÷10 ራዕ 3÷20 የእያንዳንዱ የክርስቲያኖችን ሰውነት የሚያመላክት ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ እንደሆናችሁ አታውቁምን›› 1ኛቆሮ. 3፡101

# የቤተ ክርስቲያን አሠራርና ክፍሎች







## ሀ/ የቤተ ክርስቲያን አሠራር

በኢዮጵያ ኦርቶዶክስ ጠዋህዶ ቤተክርስቲያን በገጠርና በከተማ ሦስት ዓይነት የቤተክርስቲያብ አሠራር አለ እነርሱም

1 ክብ / ቤት ንጉሥ /

ቅድስት ቅኔ ማህሌት መቅደስ በግድግዳ የተከፈለ ነውመግቢያው ሶስት በሮች ሲኖሩት
በስተሰሜን ያለው በር የወንዶች መግቢያ ነው።
በስተደቡብ ያለው በር የሴቶች መግቢያ ነው።
በስተምሥራቅ ያለው በር የካህናት መግቢያ ነው።
አንድ ጉልላት አለውነው።

2 ሰቀላ /ምኩራብ/

ከሰለሞን ቤተ መቅደስ የተወሰደ ንድፍ ሲሆን አራት ማዕየንነት ያለው ዘመስቀል ቅርጽ ነው
መቅደስ ቅድስት ቅኔማህሌቱ በግድግዳ የተከፈለ ሳይሆን በመጋረጃ እና በአእማድ የተከፈለ ነው

3 ዋሻ

ቅድስት ቅኔ ማህሌት መቅደስ በመጋረጃ ዘተከፈሉ ናቸው ብሩም አንድ ኒው

## ለ/ የቤተክርስቲያን ክፍሎች

በኢዮጵያ ኦርቶዶክስ ጠዋህዶ ቤተክርስቲያን ስርዓት መሠረት ቤተክርቲያን ውስጡ በሦስት ይከፈላል እነርሱም

**1 / መቅደስ (ቅድስተ ቅዱሳን)** **2 / ቅድስት** **3/ ቅኔ ማሕሌት** ናቸው ።

1 መቅደስ (ቅድስተ ቅዱሳን)

ሚስጢረ ቁርባንና የሚፈፀምበት፣መንበረ ታቦት የሚገኝበት፣ሌሎች ንዋየ ቅዱሳት የሚገኝበት፣ይህ ስፍራ ስልጣነ ክህነት ያላቸው ብቻ የሚገቡበት ነው።
በዚ ክፍል ፦

ፓትሪያርክ (ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት) ፣ ሊቀ ጳጳሳት
ጳጳሳት፣ ኤጴስ ቆጶሳት ይገኙበታል።

መቅደስ ፫ (ሶስት) በሮች አሉት፦
ሰሜን ፣ ደቡብ ፣ምዕራብ
ለእያንዳንዱ በር መጋረጃ ኣለው፣

መቅደስ ፩(ኣንድ) ጉልላት ኣላት።

2 ቅድስት

ስያሜው ከብሉይ ኪዳን ተመሳሳይነት ኣለው፣የቤተክርስቲያን ማዕከላዊ ቦታ ነው፣
በስተምዕራብ ቆመው የሚያስቀድሱ፦
ቆሞሳት፣ቀሳውስት፣ዲያቆናት ናቸው።
በስተሰሜን ቆመው የሚያስቀድሱ፦
መኖኮሳት፣የሚቆርቡ ወንዶች ናቸው።
በስተደቡብ ቆመው የሚያስቀድሱ፦
ደናግል መኖኮስያት፣የካህናት ሚስቶች፣የዲያቆናት ሚስቶች ናቸው።

በቅድስት ስርኣት ቁርባን ይፈጸማል(ለመእመናን) ስርኣተ ጥምቀት ይፈጸምበታል። ፬(ኣራት)በሮች ሊኖሩት ይገባል።

3 ቅኔ ማሕሌት
ቤተክርስቲያን ሲገቡ የሚገኘው የመጀመሪያ ክፍል፣ስርዓተ ማህሌት ይከናወንበታል፣
በቅኔ ማህሌቱ ሰሜናዊ ምስራቅ በኩል(ቀሳውስትና ዲያቆናት ይሆናሉ)
ቀሳውስትና ዲያቆናት በመንፍቀ ሌሊት በነግ(በጥዋት) ሰዓታት ይቆሙበታል፣ ኪዳን ያደርሡበታል፣
ለጥምቀተ ክርስትና እና ለቁርባን ያልበቁ ንኡስ ክርስቲያን ይቆሙበታል፣ወንዶች መእመናን ቁመው የሚያስቀዱሱበት ቦታ፣
መዘምራን በሚዘምሩበት በቅኔ ማህሌት ቁመው የሚያስቀድሱ ንፍቀ ዲያቆናት፣ ኣናጉስጢስ፣ መዘምራን ናቸው።
ቅኔ ማህሌቱ በደቡባዊ ምስራቅ በኩል የሚገኘው ቦታ የሴቶች መቆሚያ ነው፣
በቤተክርስቲያናችን ስርዓት ወንዶችና ሴቶች ኣብረው ቆመው መጸለይ ስለማይችሉ በመጋረጃ ይከፈላል።
በምስራቅ የካህናት መግቢያ ነው፣
በሰሜን የወንዶች መግቢያ ነው፣
በደቡብ የሴቶች መግቢያ ነው።

## ንዋያተ ቅድሳት

### 1 የቤተ መቅደስ ንዋያተ ቅድሳት

**ታቦተሕግ (ጽላት)**
ጽላት እግዚአብሔር አምላካችን ለሙሴ አስቀድሞ አሰርቱ ቃላትን በእጁ ጽፎ የሰጠው ቃሉ ተጽፎ የሚገኝበት ነው።ታቦትየሚባለው ጽላቱ የሚቀመጥበት ማደሪያ ነው። በአሁኑ ጊዜ ታቦትና ጽላት በአንድ ይጠራሉ።



**መጾርመስቀል**
የመጾር መስቀል በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ በዲያቆናት እጅ እንዲሁም በካህናት ለቡራኬ የሚይዙት ሲሆን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሰበን (መግነዝ) ለሐዋርያት በእርገቷ ጊዜ የሰጠቻቸው ምሳሌ የሆነ አብሮ የሚንጠለጠልበት መስቀል

**የእጅ መስቀል** ካህኑ በቅዳሴ ጊዜ የሚይዘው መስቀል

#### የቀሳውስት አልባሳት

**ቀሚስ**
በጥንት ዘመን አብደላከኒ የሚባል የካህናት ቀሚስ ነበር፤ አሁን ግን ጌጥነት ካላቸው ጨርቆች የሚሰራ ነው።
**ካባ ላንቃ**
ከካባው ጋር ለምድ አብሮ ተሰፍቶ ስለሚገኝ ነው "ካባ ላንቃ" የተባለው።
**ሞጣእት**
በአንገት ተጠልቆ ፊት ለፊት የሚወርድ የደረት ልብስ ነው።
**ቆብ /ቀጸላ/**
በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ካህኑ ወይም ቄሱ በራሱ ላይ ደፍቶ የሚገባው ነው።

#### የዲያቆናት ልብስ

**ቀሚስ**
ጌጥነት ካላቸው ጨርቆች የሚሰራ ነው። በመጀመሪያ የሚለበስ ልብስ ነው፤ በልክ እንዲሆን የታዘዘ ሲሆን ከረዘመ ማሳጠሪያ፣ ሰውነትን ማጠንከሪያ የሚሆን መታጠቂያ አለው።
**ለምድ ላንቃ**
በቀድሞ ዘመን ቀሚሱ ለብቻ ለምዱ ለብቻ ይዘጋጅ ነበር። አሁን ግን ለምዱ ከቀሚሱ ጋር አብሮ የሰፋል።
**ከፋይ ድግድጋት**
ከግብጽ ቤተክርስቲያን የተወሰደ ሲሆን ዲያቆናት አንዳንድ ጊዜ ለምድና ቀሚስ በመልበስ ፋንታ ቀሚስ ለብሰው በከፋይ መታጠቂያ በመስቀለኛ ቅርጽ ስለሚታጠቁና ስለሚያደገድጉ ከፋይ ድግድጋት ይባላል።
**አክሊል (ቆብ)**
በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ዲያቆን አክሊል ወይም ቆብ አድርጎ ይቀድሳል።
**መንጦላዕት**
ሦስቱም የመቅደስ በር የሚጋረዱ መጋረጃዎች ናቸው። እነርሱም የመቅደሱን ክብር የሚሰጡ ናቸው። መጋረጃዎቹ የሚከፈቱበትና የሚዘጉበት ጊዜ አለ። በመጀመሪያ ቅዳሴ "አእኑየ" ከሚለው ምዕዳን ጀምሮ እስከ "ሚመጠን" እስከሚለው ድረስ ይዘጋል። "ስግዱ" ተብሎ ከታወጀ እና "ፍትሐት ዘወልድ" እና "በእንተ ቅድሳት" ሲጸለይ ከተከፈተ ጀምሮ እስከ ፍሬ ቅዳሴ ድረስ ይከፈታል። ከፍሬ ቅዳሴ እስከ ሦስተኛው "ጸሎተ ፈትቶ" ማለትም "አርህዉ ኆኅተ መኳንንት" ብሎ ንፍቁ ዲያቆን ማሳሰቢያ እስከሚሰጥ ድረስ ይዘጋል። "አርህዉ ኆኅተ መኳንንት" ሲል ይከፈታል፣ በቁርባን ጊዜ ይዘጋል።
**ልብሰ ታቦት (መጎናጸፊያ)**
ይህ ለአክብሮተ ሥጋውና ደሙ በቅዳሴ ጊዜ መንበሩ ወይም መሰዊያው የሚለብሰው፣ ታቦት በወጣ ጊዜ የሚጎናጸፈው ነው። ስለዚህ ስሙ መጎናጸፊያ ይባላል።

**መንበረ ታቦት**
መንበር የታቦት ወይም የጽላት መቀመጫ ዙፋን ነው። መሥዋዕተ ኦሪቱ ይቃጠልበት፣ ይሰዋበት በነበረው ፈንታ መንበሩ ይገባ ስለነበር ከታቦቱ ጋር "መሰዊያ"ይባላል።

**ጻሕል**
የከቡር ሥጋው ማስቀመጫ እና ማክበሪያ ነው። ይኸውም ከወርቅና ከብር፣ ከነሐስና ከብረት የሚሰራ ነው። የተለየ ቅርጽ የተለየ ምልክት ያለው

**ማኅፈዳት**
አምስት የልብስ መጠቅለያዎች ወይም መሸፈኛዎች ናቸው። ብዙውን ጊዜ በጥቁር ጨርቅ የሚሰሩ ናቸው። አንደኛው ከጻሕሉ ስር በታቦቱ ላይ ይነጠፋል፤ ሁለተኛው በጻሕሉ ላይ ይነጠፋል፤ ኅብስቱ የሚጠቀለልበት ነው፤ ሦስተኛው የመሥዋዕቱ ልብስ ነው፤ ቁመቱ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ሆኖ ይለብሳል። አራተኛው ከሰሜን ወደ ደቡብ ሆኖ ይለብሳል፤ አምስተኛው ከሰሜን ምስራቅ (መስዕ) ወደ ደቡብ ምዕራብ (አዜብ) ሆኖ ይለብሳል።
ምሥጢሩ፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በከብቶች በረት ሲወለድ በጨርቅ መጠቅለሉንና በበለስ ቅጠል መሸፈኑን የሚያስረዳ፤ አንድም ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በድርብ በፍታ የገነዙትን የሚያመለክት ነው።

## ጽዋዕ
የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ደም የሚቀርብበት ንዋየ ቅዱስ ነው።
ከወርቅ ከብር ከመዳብ ከነሐስ ወይም ከብረት የሚሰራ ነው።



**እርፈ መስቀል**
የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ለማቀበል የሚያገለግል ንዋየ ቅዱስ ነው። ይኸውም ጽዋዕ ከተሰራበት ቁስ የሚሰራ ሲሆን በደሙ በያዣ በኩል በጣም ጎድጎድ ያለ ልዩ ቅርጽም ያለበት ወደ እጅ መያዣው ጋር መስቀል ያለበት ነው።

## ዓውድ
ክቡር ሥጋው መጠበቂያና ሰፋ፣ ጎላም ብሎ እንዲታይ የሚያደርግ ነው። የሚሰራው ከብረት፣ ከነሃስ፣ ከእንጨትም ነው። ስሙ እንደሚያመለክተው አደባባይ ማለት ስለሆነ ጌታችን የተፈረደበት የጲላጦስ አደባባይ ምሳሌ ነው።

## አጎበር
በዓውዱ ላይ የሚደፋ አራት ማዕዘን ሦስት እግር ያለው እንጨት ወይም ብረት ሊሆን ይችላል። ይህም ክቡር ሥጋውን ልብሱ እንዳይነካው ከፍ አድርጎ ልብሱን የሚይዝ የሚከላከል ነው። እንዲሁም መጎናጸፊያውን ከፍ አድርጎ ክብሩን የሚገልጽ ነው።



**ጽንሐሕ**
የእጣን ማሳረጊያ ንዋይ ቅዱስ ነው። ይኸውም ከወርቅ፣ ከብር፣ ከብረት ሊሰራ ይችላል። በኦሪት የወርቅ ማዕጠንት እንዲሰራ እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘው ነው። በዚህ ምሳሌ ዛሬ ድረስ ይሰራል።

**መቅረዝ (ቀንዲል ወይንም ዘይት)**
መቅረዝ የመብራት መስቀያ ወይንም ማስቀመጫ ሲሆን ፤ከቤተ መቅደስ ንዋያተ ቅዳስት አንዱ ነው
ማቴ 5 ÷15




**መሶበ ወርቅ**
ኅብስተ ቁርባን ከቤተልሔም ወደ ቤተመቅደስ የሚመጣበት ነው። ከስንደዶ፣ አክርማ፣ ከአለላ፣ ከወርቅ፣ ከብርና ከሌሎች ከከበሩ ማዕድናት የሚሰራ ነው። መለኮትን በማኅጸኗ 9 ወር ከ5 ቀን የተሸከመችና በቤተልሔም ተጉዛ አምላክን የወለደች የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው።

**ቃጭል (ቃለ ዓዋዲ፣ መረዋ)**
በቅዳሴ ጊዜ የሚቃጨልና ድምጽን የሚሰጥ ንዋየ ቅዱስ ነው። የሚቃጨለውም ወይም የሚመታውም ወደ ቅዳሴ ሲገባ፣ "ጸዑ ንዑሰ ክርስቲያን" ሲባል፣ በእግዚኦታ ጊዜ፣ ድርገት ሲወርድ፣ በጸሎትና በምህላ ጊዜ ይቃጨላል። በሰሙነ ሕማማት ጊዜ ደውልን ተክቶ ያገለግላል።



**ደውል**
አገልግሎቱም ሌሊት የተኙትን በመቀስቀስ ለሰዓታትና ለማኅሌት 15 ጊዜ ይደወላል፤ በነግህ በ3 ሰዓት ለዋዜማ ቁመት 12 ጊዜ ይደወላል፤


## 2 የቅኔ ማኅሌት ንዋያተ ቅድሳት፡

**ከበሮ**
ከበሮ የሚለው ቃል አታሞ፣ ነጋሪት፣ ለከብረ-በአል የሚመታ፣ ትእምርተ ክብር፣ ጪሂ፣ ተሰሚ ማለት ነው።



**ጸናጽል**
ጸናጽላት በሚልበት ጊዜ ብዛትን ጸናጽል በሚልበት ጊዜ ነጠላን የሚያመለክት ሲሆን ትርጉሙም ሻኩራ፣ ቃጭል እንደማለት ነው። ጸናጽል ከነሃስ፣ ከብርና ከሌላም ማዕድን ሊሰራ የሚችል የዜማ መሳሪያ ነው። ጸናጽል ያማረ ድምጽ ያለው ሆኖ መልክና ልዩ ጌጥ አለው። መዝ. 150÷5"ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት።

**መቋሚያ**




መቋሚያ ማለት መደገፊያ፣ መመርኮዣ ማለት ነው።በመሆኑም ቅዱስ ያሬድና አባ እንጦንስ በማኅሌትና በጸሎት ወይም በሰዓት ጊዜ መቋሚያ እንዲያዝ አድርገዋል። በመሆኑም ቅዱስ እንጦንስ በጸሎት ጊዜ፤ ቅዱስ ያሬድ በማኅሌት ጊዜ መቋሚያን ተጠቅመዋል።

# ፩ ጾም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምኅሮ መሠረት ጾም በሁለት ይከፈላል፡፡

፩. የዐዋጅ /የሕግ/ ጾም በዐዋጅ ለሕዝቡ ተነግሮ ሕዝቡ በሁሉ ዐውቆት በአንድነት የሚጾመው ጾም የዐዋጅ ጾም ይባላል፡

፪. የግል ጾም

ምእመናን በግል ወይም በማኅበር ወስነው ሊጾሙት ይችላሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይህን ዓይነቱን ጾም ገዳማውያን፣ መነኮሳትና ባሕታውያን ይጾሙታል፡፡ ጾመ ጽጌ (የጽጌ ጾም ከመስከረም ፳፮—ኅዳር ፮) ጾመ ዮዲት

## ፯ቱ የአዋጅ አጽዋማት

በቅድስት አገራችን በኢትዮጵያ መላው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በማኅበር የሚጾማቸው ሰባት የአዋጅ አጽዋማት አሉ። እነርሱም፡-

**፩ኛ- ጾመ ነቢያት/ የነቢያት**

ከጌታችን ከአምላካችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን በፊት ባሉት አርባ ቀናት ውስጥየሚጾም ነው።

**፪ኛ- ጾመ ነነዌ/የነነዌ ጾም/፡-**

ሕዝበ ነነዌ የጾሙት እና መልስ ያገኙበት ለሦስት ቀናት የሚጾም ነው።

**፫ኛ- ዐብይ ጾም/ጾመ ኢየሱስ/፡-**

እንዲሁም ሁዳዴ ወይንም ጾመ አርባ ይባላል።ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ ለአርባ ቀናት የጾመው ነው። ከጾሙ መጀመርያ ያለው ሳምንት ጾመ ሕርቃል እንዲሁም የመጨረሻው ሳምንትን ሰሞነ ሕማማትን ጨምሮ ለስምንት ሳምንታት የሚጾም ነው።

የዐቢይ ጾም ሳምንታት

| | | |
|---|---|---|
| 1ኛው እሁድ ዘወረደ /ጾመ ሕርቃል / | 2ኛው እሁድ ቅድስት | 3ኛው እሁድ ምኩራብ |
| 4ኛው እሁድ መጻጉዕ | 5ኛው እሁድ ደብረዘይት | 6ኛው እሁድ ገብርሔር |
| 7ኛው እሁድ ኒቆዲሞስ | 8ኛው እሁድ ሆሳዕና | 9ኛው እሁድ ትንሳኤ ናቸው። |

**፬ኛ- ጾመ ሐዋርያት/የሐዋርያት ጾም/፡-**

ከበዐለ ጰራቅሊጦስ ማግስት ከሰኞ ቀን ጀምሮ የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመታሠቢያ በዓል እስከሚከበርበት ሐምሌ ፭ ቀን ድረስ ይጾማል። ይኸ ጾም እንደ ሌሎቹ አጽዋማት የተወሰነ ቁጥር የለውም። የትንሣኤ በዓል በመጀመርያው የሚያዝያ ወር ቀናት ሲውል እና በመጨረሻው የሚያዝያ ወራት ሲውል ቁጥሩ ከፍ እና ዝቅ ይላል። ሆኖም ግን በጣም ከፍ ሲል ለ፵፱ ቀናት በጣም ዝቅ ሲል ለ፲ ፩ ቀናት የሚጾም ነው።

**፭ኛ- ጾመ ፍልሰታ/ጾመ ማርያም/፡-**

የእመቤታችን የትንሣኤዋ በዓል የሚከበርበት፤ ለሁለት ሳምንታት ያህል የሚፆም ነው።

**፮ኛ- ጾመ ድኅነት፡- /ረቡዕና ዓርብ/-**

ከትንሣኤ እስከ በዓለ ጰራቅሊጦስ ባሉት ረቡዕና ዓርብ ውጪ ዓመቱን በሙሉ ባሉት ረቡዕና ዓርብቀናት ይጾማል። ምክንያቱም ጌታን ለመያዝ ረቡዕ መክረው ዓርብ ስለሰቀሉት መከራውን ለማሰብየሚጾም ነው።

**፯ኛ- ጾመ ገሐድ/ጾመ ጋድ/፡-**

በየዓመቱ ከበዓለ ጥምቀት በፊት ያለው ቀን ይጾምና የጥምቀት ዕለት ግን ረቡዕም ሆነ አርብ ቢውል አይጾምም። ስለዚህም ጾመ ገሐድ ለአንድ ቀን የሚጾም ነው።

### የምንጾመው ከምንድነው?

ከምንመገባቸው

ከጥሉላት ምግብ ፡- ሥጋ እና ሥጋ ነክ ከሆኑ፣ ወተትና ወተት ነክ ከሆኑ፣ እንቁላል እና እንቁላል ነክ ከሆኑ

ከሚያስክር መጠጥ

ዐይን ክፉ ነገር ከማየት

ጆሮን ክፍ ነገር ከመስማት

አንደበትን ክፉ ነገር ከመናገር

እጅና እግር ክፉ ነገር ከመሥራት መጾም አለብን ።




### የማይጾምባቸው ጊዜያት

ከትንሳኤ ጀምሮ ሃምሳውም ቀን በሙሉ በዓል ነው፡፡ በዓል ስለሆነም እንደ ፋሲካ ስልሆነ ረቡዕና አርብ ቢሆን እንኳን አንጾምበትም፡፡ በበዓልነቱ ጾም እንዲሁም ስግደትም ተሽሯል፡፡

### የሚበሉ የማይበሉ እንስሣት

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከለሎቹ አብያተክርስቲያናት ልዩ የሚደርጋት ምእመኖችዋ ከክረቶስ ልደት በፊት የአይሁድን እምነት ይከተሉ ነበር። ማለትም ቀድሞውንም እግዚአብሔርን የሚያምን ሕዝብ በክርስቶስን የተቀበለ ሰለሆነ አመጋገባችን ፣አለባበሳችን፣ ባሕላችን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

በእኛ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር አምላካችን በብሉይ ኪዳን ያዘዛቸውን ትእዛዛት ሁሉ አሁንም ይከበራሉ።

ለምሳሌ ግዝረት (ዘፀ. 12፥48)
ቀዳሚትን ሰንበትን ማክበር (ዘፀ. 12)
ለአራስ ሴቶች የመንጻት ወራትን መወሰን (ዘሌ. 12) የመሳሰሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡
ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የሚበሉና የማይበሉ እንስሳት ተለይተው በቤተክርስቲያናችን ተደንግግዋል ።
„እናንተ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፤ ለአምላክህ ለእግዚአብሔ አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና፥ በምድርም ላይ ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ለራሱ ሕዝብ ትሆንለት ዘንድ እግዚአብሔር አንተን መርጦአልና ።ዘዳ 14፣1“

## የሚበሉ እንስሳት



ከቤት እንሣት በሬ፣ በግ ፣ ፍየል *።ዘዳ 14፣1*
ከዱር እንሣት አጋዘን ድኩላ ሚዳቋ ወዘተ*።ዘዳ 14፣1*
በአጠቃላይ የሚያመሰኩ እና ሰኮናቸው ስንጥቅ የሆኑትን ትበላለህ ።


## የማይበሉ እንስሳት

ፈረስ አህያ ድመት ውሻ *።ዘዳ 14፣1*
**አሳማ** ሰኮናው ስንጥቅ ነው ነገር ግን አያመሰኳም **ስለዚህ ሥጋው አይበላም።**
**ጥንቸል** ያመሰኳል ግን ሰኮናው ስንጥቅ አይደለም ስለዚህ ሥጋው አይበላም።



የመሳሰሉት አይበሉም
ከሚበሩ የማይበሉት ንስር፣ገዴ ፣ ቁራ፣አሳ አውጭ፣ሰጎን የሌሊት ዎፍ ፣ ዳክየ፣ዝዬ፣ጉጉት፣ ጥንብ አንሳ አይበሉም በተጭማሪ *ዘዳ 14፣1 አንብብ*
በውኆች ውስጥ ከሚኖሩት ሁሉ የምትበሉአቸው እነዚህ ናቸው፤
ክንፍና ቅርፊት ያላቸውን ትበላላችሁ።ክንፍና ቅርፊትም የሌላቸውን አትበሉም፤ ለእናንተ ርኩስ ናቸው።
*ዘዳ 14፣1 አንብብ*





## ፯ ጸሎት

### ፯ቱ የጸሎት ጊዜያት



1. ነግኅ (ማለዳ ጧት)፡-(6:00)- መዝ.5÷3፡- ‹‹በማለዳ ድማፄን ትሰማለህበማለዳ በፊትኽ እቆማለሁ›› ብሎ ነብየ እግዚአብሔር ለጸሎት እናለምሰጋና በፊቱ እንደቆመ ሁሉ አምላካችን እግዚአብሔር ሌሊቱንበሰላም እና በምህረት ጠብቆ የማለዳውን ብርሃን እንድናይ ስለረዳንእናመሰግነዋለን፡፡
2. ሠለስት (ሦስት ሰዓት)፡-(9:00)



በዚህ ሰዓት የሁላችንም እናት ሔዋን የተፈጠረችበት ሰዓት ነውና(ዘፍ.2÷21-24) እናቶቻችን ፣የትዳር አጋሮች፣እህቶች፣ሴት ልጆች የማግኘታችን መሠረት ነውና በዚህ ሰዓት እግዚአብሔር አምላካችንእናታችን ሔዋንን ስለፈጠረልን እናመሰግነዋለን፡፡
3. ቀትር (ስድስት ሰዓት)፡- (12:00)



በዚህ ሰዓት ፀሐይ ስትበረታ ሰውነታችን ሲዝል አዕምሮአችን ይሰንፋልእና አጋንንት ይበረታሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ሰውነታችንን አበርትተንህሊናችንን ሰብስበን ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፡፡(መዝ.54÷17፤90÷6)
4. ተሰዓት (ዘጠኝ ሰዓት) (15:00)



በዚህ ሰዓት ቅዱሳን መላዕክት የሰው ልጅ የጸለየውን፣ጸሎት፣ልመና፣እጣን፣የሠራውን ሥራ ሁሉ የሚያሳርጉበት ሰዓት ነው፡፡ (የሐዋ.10÷3)
5. ሠርክ (ዐሥራ አንድ ሰዓት)(17:00)በዚህ ሰዓት ላይ ሰው ሁሉ ሥራ ሠርቶ ከሥራው የሚያርፍበት እናዋጋውን የሚቀበልበት ሰዓት ሲሆን እኛም ምግባር ቱሩፋት ሰርተ ዋጋችንን ከአምላካችን የምንቀበልበት ሰዓት ነው፡፡ (ማቴ.20÷1-16)



6. ንዋም (የመኝታ ሰዓት) (19:00)
በዚህ ሰዓት ቀኑን ሙሉ ስንወጣ ስንወርድ የጠበቀንን አምላክ አመሰግነን፤ ዳግመኛም የሌሊቱን ሰዓት ባርኮ የሰላም እንቅልፍ ይሰጠን ዘንድ ለጸሎት እንቆማለን፡፡



7. መንፈቀ ሌሊት (0:00)
ይህ ሰዓት ታላቅ ሰዓት ነው፡፡ አምላካችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት፣ የተጠመቀበት፣ ከሙታን መካከል ተለይቶ የተነሣበት ዳግመኛም በህያዋን እና በሙታን ለመፍረድ የሚመጣባት ሠዓት ስለሆነች ይህን ሁሉ በማሰብ እና እግዚአብሔር ለእኛ ሲል ያደረገዉን ነገር ሁሉ በማሰብ የሚጸለይበት ሠዓት ነው። -(ሉቃ.2÷7-8፤3÷21.ዮሐ.20÷1፤ማቴ.25÷6፤ማር.13÷35)



### የግል ጸሎት

ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ በጸሎት በቤታቸው ሆነ ከቤት ወጭ ከአምላካቸው ጋር መገናኘት አለባቸው።ስለዚህ በቀን የተወሰነ ሰዓት መድቦ ስለ ራሱ፣ ሰለ ሌላ ሰው /ባልንጀራ/ ስለ ሀገሩ፣ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ዕለት ሥራው፣ ወዘተ መጸለይ አለበት። 7ቱ የጸሎት ጊዜያትም የግል ጸሎት የምናደርስባቸው ጊዜያት ናቸው።

### የጋራ ጸሎት

አባቶቻችን ሐዋርያት በኅብረት ሆነው ለጸሎት ይተጉ እንደነበረው（የሐዋ. 8፣2）በኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የምእመናን አንድነት እንዲኖር ጸሎተ ምሕላ፣ ጸሎተ ኪዳን፣ ቅዳሴ፣ ሰዓታትና ማኅሌትን በመሳሰሉት የአንድነት ጸሎተ ሥርዓቶች መካፈል አለብን። በማኅበር ጸሎት ጊዜ የግል ጸሎት ማድረግ ተገቢ አደለም።

### የምንጽልያቸው የጸሎት ዓይነቶች

ጸሎታችን ደግሞ አባቶቻችን ጸልየው በረከትን ያገኙበትን ጸሎት ቢሆን መልካም ነው ።
ለምሳሌ ከብዙው መከክል
የዘወትር ጸሎት
አአትብ ገጽየ
ነአኩተከ እግዚኦ
አቡነ ዘበሰማያት
በሰላመ ቅዱስ
ጸሎተ ሃይማኖት
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ
ስብሀት ለአብ
ሰላም ለኪ
ጸሎተ እግዝእትነ
የየቀኑን ወዳሴ ማርያም
መልኮችንና መዝሙረ ዳዊትን
ጸሎተ ነቢያትን



## ፫ ስግደት

### ሀ/ የስግደት አፈጻጸም

**የመጀመሪያው የስግደት አፈጻጸም** ሥርዐት መሬት ላይ በመውደቅ ወይም ሙሉ በሙሉ ተደፍተው የሚሰግዱት ስግደት ሲሆን በልዩ ስሙ # **ወዲቅ** በመባል ይታወቃል፡፡
ከዚህ በተጨማሪ "ፊቱንም ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ" /ዘፍ.19፡1/
"ሰገደም በግንባሩም ተደፋ" /ዘኁ.22፡31/
"በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደ" /ኢያ.5፡13/
"ማቅ ለብሰው በግንባራቸውተደፉ" /1ኛ ዜና.21፡16/
"በፊቱ ወደ ምድር ተደፉ" /2ኛ ነገ. 2፡15/ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ወዲቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የስግደት ዐይነት መሆኑንየሚያስረዱ ናቸው፡፡

**ሁለተኛው የስግደት አፈጻጸም አስተብርኮ** /በመባል ይታወቃል፡፡ ይህም ስያሜው እንደሚጠቁመው ጉልበትን ሸብረክ በማድረግ፣ በጉልበት በመቆም ወይም በመንበርከክ የሚፈጸምነው፡፡

**ሦስተኛው የስግደት አፈጻጸም አድንኖ** ይባላል፡፡አድንኖ ራሥን፣ ግንባርን፣አንገትን ዝቅ በማድረግ የሚሰገድ ነው - "አድንኑ አርእስቲክሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ..." እንዲባል በቅዳሴ፡፡ ይህም እንደቀደሙት ሁለቱ የስግደት አፈጻጸም ዐይነቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ነው፡፡ በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 49 ቁጥር 23 ላይ "ግንባራቸውን ወደ ምድርዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል" ይላል፡፡ ካህናትም "በንስሐ ውስጥ ያላችሁ ራሣችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ" ማለታቸው አድንኖን በመፈጸም ስገዱ ሲሉን ነው፡፡

ወዲቅም፣ አስተብርኮም ሆነ አድንኖ የስግደት አፈጻጸም ዐይነቶች ናቸው እንጂ ከስግደቱ ዓላማ ጋር ወይም ከሚሰገድለት አካል አንጻር የሚፈጸሙ አይደለም፡፡ በሌላ አገላለፅ ሦስቱን የስግደት ዐይነቶች ስግደት ለሚገባው ሁሉ እንፈጽማለን - ሦስቱንም ዐይነት ስግደት ለእግዚአብሔርም ለቅዱሳንም እናቀርባለን፡፡ ነገር ግን የመስገዳችን ምሥጢሩ ይለያያል፡፡ ይህንንም እንደሚከተለው እንየው፡፡ስንዱዋ እመቤት ቅድስት ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ ከዓላማው አንፃር ሁለት ዐይነት ስግደት እንዳለ ታስተምራለች፡፡

### ለ/የስግደት ዐይነቶች

በቤተክርስቲያናችን ሁለይ ዓይነት ስግደት አሉ አነርሱም የአምልኮ ስግደትና የጸጋ ስግደት ናቸው

## 1 የአምልኮ ስግደት

ይህ የስግደት ዓይነት የሚሰገደው ለአምላካችን ብቻ ነው ።የእምነት ስግደት ስለሆነ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ /ተወልዶ/ መከራን ተቀብሎ በመስቀል ተሰቅሎ በሞቱ ሞታችንን ሞቶ ከሲኦል አውጥቶን ከሙታን ተነስቶ ማረጉን እያሰብን እንዲሁም አሁንም ላደረገልን ወደፊትም ለሚያደርግል መልካም ነገር ሁሉ እያመሰገንን የምንሰግደው የአምልኮ ስገደት ነው።

## 2 የጸጋ ስግደት

ይህ የስግደት ዓይነት የሚሰገደው በተለይ ለቅድስተ ቅዱሳ ለእምቤታችን ለድንግል ማርያም ፣ የመዳናችን ምክያት ለሆነችው በረከቷ፣ ፍቅሯ፣ እንዲያድርብን ለምኝልን እያልን ስንለምን የምንሰግደው የጸጋ ስግደት ነው።
የመላእትን ተራዳኢነት ስንለምን የምንሰደው የጸጋ ስግደት ነው።
ጻድቃን ሰማእታትን ስንማጸን የምንሰግደው የጸጋ ስግደት ስግደት ነው።

### የሚሰገድባቸው ጊዜያት

**1ኛ. በጸሎት ጊዜ ስግደትን ከሚያነሣ አንቀጽ ሲደርስ**
በቅዳሴ ጸሎት ጊዜ ዲያቆን ስግዱ ሲል ይሰገዳል
ስለዚህ በጸሎት ጊዜ ስግደትን የሚያነሣ ንባብ ስናገኝ እንዲሁም ስግደትን የሚያነሣ ንባብ ባናገኝም መስገድ ከስድስቱ የጸሎት ይዘቶች አንዱ ነውና መስገድ ይገባል፡፡
**2ኛ. በጾም ወራት**
ጾም የሚቀደሰው በጸሎት ፣ በምጽዋት ፣ በዕንባና በስግደት ነው፡፡ ስለዚህ በጾም ወራት ጾማችንን ቅዱሱ የሚቀበለው ቅዱስ ጾም ለማድረግ መስገድ ተገቢ ነው፡፡
**3ኛ. በሰሙነ ሕማማት**
ሰሙነ ሕማማት በጾም ፣ በጸሎት ፣ በስግደት የሚከበር ልዩ በዓል ነው፡፡ ጾሙም ስግደቱም ጸሎቱም የሚበረታበት የመጨረሻው የዐቢይ ጾም ሳምንት ነው፡፡
**4ኛ. በቅዳሴ ጊዜ**
በቅዳሴ ጊዜ መስገድ እንደሚገባ "ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሐት" ፣ "ንስግድ" ፣ "አድንኑ አርእስቲከሙ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ" ፣ "በንስሐ ውስጥ ያላችሁ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ" ሲባል መስገድ አለብን።
**5ኛ. በንስሐ ጊዜ**
"በንስሐ ውስጥ ያላችሁ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ" የሚለው ንባብ በንስሐ ውስጥ መስገድ እንደሚገባ የሚያመለክት ነው፡፡ የንስሐ አባቶች በንስሐ ውስጥ ላሉ ልጆቻቸው ስግደትን ቀኖና አድርገው መስጠታቸው ነው፡፡ ስለዚህ ስግደት የንስሐ ሕይወት አንዱ አካል ነው፡፡
**6ኛ. ስንሳለም**
ቤተ ክርስቲያንን ስንሳለም መስገድ ተገቢ ነው፡፡ ስንሳለም እንዲህ እያልን ነው፡-
"ሰላም ለኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ አምሳለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፣ ማኅደረ መለኮት፣ ምስኣል ወምስጋድ ወመሥተሥርየ ኃጢአት"
ስንሳለም በምንናገረው አጭር ጸሎት ውስጥ "...ምስአል ወምስጋድ" ማለታችን መስገድ እንደሚገባን የሚጠቁም ነው፡፡ መስቀልን ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ፣ ቅዱሳት ሥዕላትን ፣ ቅዱሳት ቦታዎችን ፣ ...ወዘተ ስንሳለም በተመሳሳይ መልኩ መስገድ ተገቢ ነው፡፡

### የማይሰገድባቸው ጊዜያት

የሚሰገድባቸው ጊዜያት እንዳሉት ሁሉ የማይሰገድባቸው ጊዜያትም አሉ፡፡ እነዚህ ስግደት የተገዘተባቸው ጊዜያት የሚከተሉት ናቸው፡፡
**1ኛ. በዕለተ እሑድ**
ጌታ የተነሣባት ፣ ዳግምም የሚመጣባት ዕለት ናት፡፡ በዚህና በሌሎች ምክንያቶችም ሰንበተ ክርስቲያን እሑድ በዓል ነች፡፡ ስለዚህ በዕለተ እሑድ መስገድ የተከለከለ ነው፡፡
**2ኛ. በበዓለ ሃምሳ ወራት**
ከትንሳኤ ጀምሮ ሃምሳውም ቀን በሙሉ በዓል ነው፡፡ በዓል ስለሆነም እንደ ፋሲካ ስልሆነ ረቡዕና አርብ ቢሆን እንኳን አንጾምበትም፡፡ በበዓልነቱ ጾም እንደተሻረበት ስግደትም እንዲሁ ይሻርበታል፡፡
**3ኛ. በጌታችን በዓላት**
በእሑድና በተከበሩት በዓላት ቀን ስግደት አይገባም፤ እነዚህም ትስብእት/ጽንሰት ፣ ልደት ፣ ጥምቀት ፣ ሆሣዕና ፣ ትንሣኤ ፣ ዕርገት ፣ በዓለ ሃምሳ ፣ ደብረ ታቦር ናቸው ።
**4ኛ. የእመቤታችን በዓላት**
በእመቤታችን በዓላትም ስግደት የተከለከለ ነው፡፡
**5ኛ. ሥጋውንና ደሙን ከተቀበሉ በኋላ**
ሥጋውና ለክቡር ደሙ ክብር ስንል ከተቀበልን በኋላ ዝቅ ብለን አንሰግድም፡፡
**6ኛ. በ12 ፣ በ21 ፣ በ29**
በ12 ሚካኤል በ21 ማርያም በ29 ደግሞ በዓለ ወልድ ስልሆነ አይሰገድም።

# ቤተክርስቲያን ምንድን ናት ?

ሀ/ ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤት ናት “ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች” ማር 11፡1-17

ለ/ ቤተ ክርስቲያን የስግደት ቤት ናት፤ ለእግዚአብሔር ይሰገድባታል፡፡ “እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ።” መዝ 5፡7፡፡

ሐ/ ቤተ ክርስቲያን የመሥዋዕት ቤት ናት፡፡ “ይህ ሕዝብ በእግዚአብሔር ቤት መሥዋዕትን ያቀርብ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ቢወጣ…” ቀዳ ነገ 12፡

መ/ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ናት ስሙ ይጠራባታል፣ እግዚአብሔር ያድርባታል፣ ተአምራቱን ያሳይባታል፡፡“ዳዊትም፡- ይህ የእግዚአብሔር ቤት ነው፥ ይህም ለእስራኤል ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነው መሠዊያ ነው አለ።” ቀዳ ዜና 22፡1፡፡

ሠ/ ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር መገናኛ ናት፣ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኙባታል፡፡ “በእግዚአብሔር ቤትበመቅደሱ ውስጥ እንገናኝ፡፡” ነህ 6፡ 10፣ ዘጸ 29፡43፡፡

# ቤተ ክርስቲያን ለምን ይኬዳል ?

ሀ/ ለጸሎት፡፡ ሁ/ ለስግደት፡፡ ሂ/ ለቅዳሴና ለቁርባን፡፡ ሃ/ ለትምህርት፡፡ ሄ/ ለምጽዋት፡፡

ህ/ ክርስቲያንነትን በአንድነት (በጉባኤ) ለመግለጽ ለመሳሰለው መንፈሳዊ ጉዳይ ሁሉ፡፡

**ቤተክርስቲያን ባህረ ጥበባትአትመረመርም እጅግ ጥልቅ ናት  የሲኦል ደጆች አይችሏትምቤተክርስቲያን አትታደስም!የ ሐዋርያት ጉባኤ ስለሆነች ስለአንዷት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላምእንማልዳለን! (መጽሐፈ ሚስጢር)**

# ወደ ቤተክርስቲያን  ስንገባ



## ማማተብ

ማማተብ ማለት "አማተበ ወይም አመሳቀለ" ከሚል የግእዝ ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጓሜውም
"ምልክት ማድረግ ወይም መባረክ" ማለት ነው።
እኛ ኦርቶዶክሳውያን በሕንጻ ቤተ እግዚአብሔር ተገኝተን እናማትባለን  እንሳለማለን፣እንሰግዳለን
አዐትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል  ሰላም  ለኪ ቅድስት ቤተክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት፡፡
፩  እጃችንን ከግንባራችን ወደ ሆዳችን ስናደርግ
ጌታችንና መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ማህፀን አደረ ስንል ነው።

፪ - (በሁለተኛ ደረጃ መሆን ያለበት) እጃችንን ከሆዳችን አንስተን ወደ ግራ ትከሻችን ከዛም ወደ ቀኝ ትከሻችን ስናደርግ - - - እኛን ከነበርንበት የሲኦል ኑሮ ወደ ገነትና እውነተኛዋ መንገድ አሸጋገረን ስንል ነው።

፫ - (በመጨረሻ የሚሆነው ) እጃችንን ከቀኝ ትከሻችን አንስተን ወደ ሆዳችን ስንመልሰው - - - ጌታችንና መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዷል እያልን ነው።

ሶስተኛውን ደረጃ ስንጨርስ የመስቀል ቅርፅ ሰራን ማለት ነው። በመስቀል መከራን: ደስታንና የዘላለም ህይወትን እናስባለን።

## ቤተክርስቲያን ስንገባ ማድረግ ያለብን

ሀ\ ያስቀየሙት ሰው ቢኖር ይቅርታ ጠይቆ::

ኀ\ የተቀየሙት ሰው ቢኖር ይቅር ብሎ ቅሬታን አውርዶ ነው::

ሐ\ በስርቆት፣ በቅሚያ፣ በማታለል የወሰዱትን የሰው ገንዘብ መልሶ ነው:: ሉቃ 19፡8::

ኸ\ መጠጥ ጠጥቶ ሰክሮ ቤተ ክርስቲያን መግባት ክልክል ነው:: ዘሌዋ 10፡3-10::

ሠ\ የታጠበ ንጹህ ልብስ መልበስ::

ሰ\ ሴቶች ከተፈጥሮ ግዳጅ ወንዶችም ዝንየት ያላገኛቸው መሆን::

ፀ\ የሚሸት ቁስል፣ የሚያነፈርቅ ጉንፋንና ሳል ይዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት አይገባም::

ጸ\ ጫማን ማውለቅ:: ዘጸ 3፡5:፣ ኢያሱ 5፡15፡

አ\ ልብስን አደግድጎ (መስቀለኛ) አድርጎ መልበስ::

ዐ\ የቤተክርስቲያን በሮች ሰአሎችን መሳም መሳለም ከገቡ በኋላ ወደ መቅደሱ መስገድ ማማተብ

እግዚአብሔር የአካል ሶስትነት አለው። በሶስትነቱ አብ ወልድ መንፈስቅዱስ ሲባል በመለኮት፣በመፍጠር፣ በስልጣን፣በአገዛዝ በፈቃድ ግን እንድ ነው።በአንድነቱ አንድ መለኮት አንድ እግዚአብሔር ይባላል። በአዳም ምክንያት ከመጣው የዘላለም ሞትና ከዲያቢሎስ ባርነት ነፃ የወጣነው ከሶስቱ አካላት በአንደኛው አካል ማለትም በወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ዶግማ ወይም እምነት ይባላል፤ መቼም ቢሆን ሊቀየር እና ሊሻሻል አይችልምና። አሻሽላለሁ የሚል ካለ ግን ቅዱሳን አባቶቻችን በሰሩት ሥርዓት መሰረት ከቤ/ክ ተወግዞ ይለያል ለምሳሌ መናፍቃን ይህን በመካዳቸው(ለማሻሻል ጥረት በማድረጋቸው) ከቤ/ክ ተለይተዋል።

## ሥ ላ ሴ

**አንድነት**

በባሕርይ፣
በመለኮት፣
በአምላክነት ፣
በሕልውና፣
በፈቃድ ፣
በፈጣሪነት፣
በአገዛዝ፣
በሥልጣን
(ዘዳ 6 ፡ 4 ኢሳ 44 ፡ 6 ኢሳ 43 ፡ 1 ዮሐ 10 ፡ 30)

**ሦስትነት**

በአካል፣
በስም፣
በግብር
(ማቴ 28 ፡ 19 1 ኛ ቆሮ 12 ፡ 4 6 ሮሜ 14 ፡ 17)

አብ:
ወላዲ (አባት)፣ አሥራፂ
አይወለድም፣ አይሰርፅም
አብ፡ አባት፣ ልብ፣ 'ከእኛ በላይ ያለው' አምላክ

ወልድ: ተወላዲ (ልጅ)
አይወልድም፣ አያሰርፅም፣ አይሰርጽም
ወልድ፡ ልጅ(የባሕርይ)፣ ቃል፣ 'ከእኛ ጋር ያለው'አምላክ፣ የእግዚአብሔር ክንዱ፣ የአብ ቀኝ እጅ

መንፈስ ቅዱስ: ሠራፂ (የሠረፀ)
አይወለድም፣ አይወልድም፣ አያሰርፅም
መንፈስ ቅዱስ፡ እስትንፋስ፣ 'በውስጣችን ያለው'አምላክ፣ የአብ ምክሩ



**ሥላሴ** አንድ ሲሆኑ ሦስት፣ ሦስት ሲሆኑ አንድ ናቸው፡፡ አንድነቱ ሦስትነቱን ሳይጠቀልለው፣ ሦስትነቱ አንድነቱን ሳይከፋፍለው በሕልውና ተገናዝበው የሚኖሩናቸው፡፡

"እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብየሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፡፡" ዮሐ15:26

„ምንም እንኳን ሥላሴን በስም፣ በአካል በግብር ሦስት ናቸው ብንልም ሦስቱ በባህርይ፣ በመለኮት፣ በህልውና፣ በፈቃድ አንድ ናቸው፡፡ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አንልም፡፡ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አካል ፍጹም ገጽ አላቸው፡፡ ነገር ግን በህልውና አንድ ናቸው፡፡"

"

"በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ፡፡" መዝ33:6

## ፬ ምጽዋዕት

ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥ከእናንተ አንዱም። በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።ያዕ 2፥16

ከላይ በያዕቆብ መለክት የሚነግረን መጾም ፣መጸለይ ፣ መስገድ፣ አግዚአብሔርን ማመን ብቻውን ዋጋ እንደሌለው ይህ ሁሉ በተግባር መተርጎም እንዳለበት ነው ። ለምሳሌ አምነት ወይንም ሃይማኖት ሲተረጎም ለተራበ በማብላት በመመጽወት ፣የተቸገረን በገዘብም ሆነ በጉልበት መርዳት ማለት ነው ። አንዲሁም ደግሞ በተጨማሪ የታመመን በመጠየቅ ፣የተጣሉትን በማስታረቅ፣አንተም የተጣላኸውን ሰው ስትምር ክርስቲያናዊነትህን ገለጽህ ማለት ነው። ይህንን ስናደርግ ጽድቅን ፈጸምን ወይንም እምነታችንን በተግባር ተረጎምን ማለት ነው። **ምጽዋት ሥርወ ቃሉ የግእዝ ቋንቋ ነው፡፡ትርጓሜውም ስጦታ፣ችሮታ፣ልግስና ማለት ነው፡፡ ሰዎች በሰዎች ላይ የሚያዩትን ችግር በማገናዘብ የተቸገሩትን መርዳት ከፍጹም ፈቃድና ርኅራኄ የሚያደርጉት ስጦታ ምጽዋት ይባላል፡፡ በፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፮ ቊ125-127 እንደተገለጠው *ምጽዋት ምሕረት ነው*፡እግዚአብሔር ከሰጪዎች ጋር የሚሰጥ ከተቀባዮች ጋር ሁኖ የሚቀበል በመስጠትና በመቀበል በሰዎች መካከል መተሳሰብና መረዳዳት እንዲኖር ሀብትን ለሀብታሞች የሚሰጠው ከእነርሱ የሚያንሱትን እንዲያስተናግዱበት ነው**

ምጽዋት፡-

ምሕረት ነው ( ፍት ነገ አንቀጽ 16 ቁ 125 )

- ለአምላክ የሚሰጥ ብድር ነው ( ለድሀ ቸርነትን የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል፤ በጎነቱንም መልሶ ይከፍለዋል፡፡ ምሳ 19፡17 )
- ብልሆች ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስቀምጡት አደራ ነው ( ሉቃ 12፡33 )፣ ( ማቴ 6፡19-21 )
- ሰው ለሰው ያለውን በጎ ፈቃድ የሚገልጥበት ክርስቲያናዊ የሥነ ምግባር ዘርፍ ነው፡፡ ( 2ኛ ቆሮ 8፡2 )
- ጠላትህ ቢራብ እንጀራ አብላው፤ ቢጠማ ውሃ አጠጣው፤ መ.ምሳሌ 25፤21

"ድሆች ከምድሪቱ ላይ አይታጡምና በአገርህ ውስጥ ላለው ድሃ ለተቸገረውም ወንድምህ እጅህን ትከፍታለህ ብዬ አዝዛለሁ" /ዘዳ15፥11/

**የጾምና የጸሎት አለመነጣጠል፡፡**

ቅዱሳን ጾምን በጠንካራ ምሽግ፣ ጸሎትን ደግሞ በጠንካራ ምሽግ ያለ ሰው በሚያጠቃበት መሳሪያ ይመስሉታል፡፡

የነነዌ ሰዎች ጾም፣ የአስቴር ጾም እና አይሁድ ከጥፋት ለመዳን የጾሙት ጾም ሁሉ ከጸሎት ጋር ነበር፡፡ዮና.2 አስቴር 2-3 እነርሱ ያገኙት መልስና ውጤቱም ጾም ከጸሎት ጋር ያለው Aንድነት መሳሪያ ነው፡፡

**ጾምና ምጽዋት አይነጣጠሉም**

ጾም ከፍቅርና ቸርነት ጋር የተያያዘ ነውና፣ ጾሚዎች ሲራቡ ለድሆችና የሚበሉት ለሌላቸው በጾም የተዉትን ምግብ እና ሌላም ለነደያን የሚያስፈልገውን ይመውታሉ፡፡እግዚአብሒርም ለነብዩ ለኢሳይያስ " እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን?.... እንጀራህን ለተራበ ትቆርስ ዘንድ÷ ስደቶኞችን ድሆችን ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ፤የተራቆተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፤ከሥጋ ዘመድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን? የዚያን ጊዜ ብርሃን እንደ ንጋት ይበራል÷ ፈውስህም ፈጥኖ ይበቅላል÷ ጽድቅህም በፊትህ ይሄዳል÷ የእግዚአብሔርም ክብር በኃላህ ይጠብቅሃል፡፡" ኢሳይ